# አማራ የሚባል ነገድ የለም ሲባል የምትበሳጩ፤አማራ ሲጨፈጨፍ ግን ዝም ለምትሉ አማራዎች ጥያቄ

*ጌታቸው ረዳ (የኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ)* getachre@aol.com

ይህ በርዕሱ የተጠቀሰ አመራ የሚባል ነገድ የለም ሲባል ሰምተው ሰማይ እስኪነካ ድረስ አቃቂራቸውን የሚያስሰሙ አማራ ነን የሚሉ በርካታ ግለሰቦች፤ "ነገር ግን" አማራው ለ24 አመት ግፍ ሲፈጸምበት ጀሮ ዳባ ብለው ቆይተው "አማራን ከፈጽሞ ጥፋት ለመከላከል የተደራጁትን አማራዎች ሲዘልፉ ከራርመው ዛሬ ደግሞ "ፕሮፌሰር መስፍን አማራ የሚባል ነገድ የለም አሉ" ብለው አዲስ መነጋገሪያ ርዕስ አድርገው ለይስሙላ "ያዙኝ -ልቀቁኝ" የሚሉ አማራዎች ተበራክተዋል።

አማራ አይደለሁም እኔ "ይሁዲ/አይሁድ" በኛ አጣራር "ፈላሻ" (ፈልሶ የመጣ የውጭ ሃይማኖት ተከታይ...ወዘተ...) ካላለን በስተቀር ይህንን ጩኸት ከሚያጦዙት መካካል አንዱ በጋዜጠኛነት ሙያ የተሰማራው ወያኔዎች የሚወዱለት በየድረገጾቻቸው ጩኸቱን እና የዜና ስርጭቶቹን የሚለጥፉለት እስራኤል አገር የሚኖር "ዜናነህ መኮንን" የተባለው ከብዙዎቹ የገደል ማሚቶዎች አንዱ ነው።

ይሁዳው ዜናነህ መኮንን "ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም" አማራ የሚባል ነገድ የለም አሉ፤ በማለት ለአማራ አዛኝ መስሎ "ይሁዲ" የሚባል ኢትዮጵያዊ ነገድ የለም ለምንል ኢትዮጵያዊያንን (ፍልስጤማዊያንን በምሳሌ እየጠቀሰ) "የደቡብ አፍሪካዊው ዲስሞን ቱቱን" ይሁዲዎቹ በፍልስጤማዊያን ህጻናት፤እርጉዞች እና ሽማግሌዎች ላይ ፋሺስታዊ ጭፍጨፋ ሲፈጽሙ በማውገዛቸው ምክንያት ሁለት መረጃዎችን ልስጣችሁ **Israelis torturing non-Jewish children. Australian documentary film. Viewer discretion. https://youtu.be/iqL048x4msM ሌላው መረጃ ደግሞ**

GAZA! Israeli Occupation And Palestinian Genocide! https://youtu.be/fBwdGP-jWj8 የይሁዲዎች ፋሺስታዊ ጭካኔን ለምን ያወግዛሉ ብለው ዲሰሞን ቱቱን ከእስራላዊያኖቹ አገር እንዳይገቡ መከልከላቸውን "ሕጋዊ እና ትክክለኛ" አርምጃ መሆኑን በምሳሌ እያጣቀሰ "በፍልስጢኤማዊያን የተፈጸመው ጨፍጨፋ ሲያሞግስ" ሲዘላብድ፤ የገደል ማሚቶ ፕሮፓጋንዳውን እያስታከከ "ይሁዲ/ይሁዲ!!!" እያለ ሲያሞግስ እንኳን ፍልስጤማዊያንን ቀርቶ በገንዘብ የተለወጡትን ኢትዮጵያዊያንን እስካሁን ድረስ በይሁዶች የተለያየ የዘረኝነት ጥቃት ሲፈጸምባቸው ዓለም የሚያውቀውን የይሁዲ "ዘረኛ ባሕሪ እና ተንኮል" (ደዊት/ዴቪድ ሆቴል የተባለው እሳራሎች ሆቴል እራሳቸው አቃጥለው ፍልስጤማዊያን አቃጠሉት" ብለው ፍስልጤማዊያንን ለመጨፍጨፍ ያደረጉትን

ወንጀል እንደተጠበቀ ሆኖ)፤ ፕሮፌሰር መስፍንም “አማራ የሚባል የለም አሉ” ማለት ይሁዲዎች የሚባሉ የሉም ከሚሉት ጋር እያነጻጸረ የተነተነውን “ወያኔያዊው አንደበቱን” ለማድመጥ “አይጋ ፎረም” በተባለው የወያኔዎች ድረገጽ ለማድመጥ ይህንን ጉግል አድርገው ያድምጡ። Zenaneh on History Writing and Prof Mesfin - ታሪክን - ማን ይጻፍ ደራሲ፡ ዜናነህ መኮነን

ይህ ይሁዲ (?) እንደሆነ የሚገመት ጋዜጠኛ፤ እውን ፕሮፌሰር መስፍንን ለመቃወም ሲል ሰፊ ትንተና ማድረጉ “ለአማራው አዝኖ፤ ወይስ እሳቸውን አስታክኮ ስለ ‘ይሁዲ” ምንነት ሊነግረን? ለነገሩ ስለ ታሪክ ማን ይጻፍ ብሎ የዘላበደው ትንትና የታሪክ አዋቂነቱን ሊነግረን ሲሞክር “ጥርስ የገባች ሀገር/ኢትዮጵያ/” የሚለው በጆን ስፔንሰር የተጻፈውን “በቅርቡ በሞት የተለዩት ሟቹ ወዳጄ ፕሮፌስር ሌቪን ነው” ብሎ ሲዋሽ መስማቱ ሰውየው ምን ያህል ታሪክ ዘጋቢ መሆኑን እራሱን አስገምቷል።

ዜናነህ መኮነን የተባለው ይሁዲ ብቻ ሳይሆን በፕሮፌሰሩ ላይ የሚጨኹ ‘በሺዎች ምናልባትም ሚልዮኖች” የሚገመቱ አማራዎች “አማራ የሚባል የለም” ብለው ፕሮፌሰር መስፍን ተናገሩ እያሉ ጸጉራቸው እስኪነጩ ድረስ በየፓልቶኩ እና በየድረገጾች ወያኔዎችም ፤ ተቃወሚዎችም ሲጽፉባቸው ታዝቤአለሁ። እኔ የሚገርመኝ እነዚህ “አማራ አለ” የሚሉና አማራ ሲገፋ ግን “ዝምን” የመረጡ “ሆዳም ያለሆኑ ከሆዳም አማራዎች ጋር የሚደመሩ” እና የፕሮፌሰሩን አጥንት ለመጋጥ የሚቃጣቸው ውሽታም ጠበቃዎች ስለ አማራው ጥቃት ምን ያህል ይሰማቸዋል? እነኚህን እና የመሳሰሉ አስመሳይ አማራዎች፤ በአገራችን ቋንቋ አጠቃቀም፤ እየሱስን ለገንዘብ የሸጡ ወይንም ይሰቀል፤ ይሰቀል ያሉ ስም ያልተገኛላቸው “ይሁዳዎች” ብዙ ናቸው።

አማራን ለማዳን በቀነ ቀጠሮ በቁጥር “100” ጊዜ ከወያኔ ፍርድ ቤቶች ተመላልሰው ነበር የተባሉት ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ የጀመሩትን እና መጨረሻ መሰዋዕት ሆነው ያደራጁትን ድርጅት “በአማራ ስም መደራጀት ወያኔነት መሆን ነው፤ አማራ ከጥቃት ድኗል እና “ኢትዮጵያ” ብለን ሰይመን እንታገል” ብለው ድርጅቱን አፍረሰው ለወያኔ “ኢላማ” መለማመጃ አድርገው ሁለንተናውን አፈራርሰው አማራ የተባለውን ሕብረተስብ ለቀጣይ እና ለማያባራ ለጥቃት ያጋለጡ ሰዎችም የተጨወቱት አፍራሽ ሚና መዘንጋት የለበትም።

እኔ ሚገርመኝ፤ “አማራ የሚባል የለም” ብለው ፕሮፌሰር ስለተናገሩ እና “አማራ አለ” ብሎ “መለስ ዜናዊ” ስለተናገረ፤ በሁለቱም ላይ ልዩነት የለም። አለ እና የለም ሳይሆን፤ አለ እያሉ አማራውን ከሕልውና ለማጣፈት የሚፈታተኑ ቡድኖች ጋር ያበሩ “ሆዳም አማራዎች” እና አማራው ሕልውናውን ሲፈታተኑት እያየ እና እየሰማ “ዝም” ብሎ ከርሞ “ፕሮፌሰር መስፍን “አማራ የሚባል የለም ስላሉ” ጸጉሩን ለመንጨት የሚቃጣ “ሆዳም ያልሆነ ከሆዳም አማራ ጋር ሚደመር አማራ” (አስመሳይ አማራ) አንድ ናቸው።

በእኔ ላይ የደረሰው የደንቆሮዎች ዘለፋ እማ ብነግራችሁ የ ኤስቅ ቢሆንም፤ ድንቁርናችን ምን ያህል መሆኑን ስንገነዘብ ግን ይከብዳል። አንድ በለመዚን ሙያ የተሰማራ ነው የሚባል ዋሺንግትነ የሚኖር "የአገው" ነገድ ነው የሚሉት "ጐጃሜ" ነኝ የሚል ሰው ፤ ከማንኛውም ኢትዮጵያ ማሕበረሰብ ሕይት ላይ በአማራ ገበሬና ኗሪ ሕይወት ላይ በከፋ መልኩ "ግልጽ ጥቃት" እየተፈጸመበት ያለው የአማራ ሕብረተሰብ የራሱ ዜጎችና ከከርሱ የተገኙ አማራዎች "ስለከዱት"፤ የቀረው አማራጭ "ራሳቸውን መከላከል" ድርጅት ያስፈልጋቸዋል፡ ብየ ስላልኩኝ እና "የትግራይ ሊሂቃን በአማራ ላይ ያላቸው የጥላቻ መነሻ " በሚል አማራ ሞረሽ ስብሰባ ተጋብዤ ጥናተዊ ጽሑፍ ስላቀረብኩኝ፤ በኔ ላይ የለጠፈው ፖለቲካው ያልገባው የዚህ ምስኪን ሰው 'ስሜን' የማጥፋት ዘመቻው በዩቱብ ላይ አሁንም ለማስረጃ ይገኛል። ነገሩ አስቂኝ ቢሆንም አንዱ እንዳለኝ "እንዳውም በይበልጥ በአማራው ሕብረተሰብ በይበልጥ እንድትታወቅ ረድቶሃል" እንዳለው ቢሆንም፤ በእግረ መንገዳችሁም፤ የዜጎች ንቃተ ሕሊና ምን ያሕል የደነቆረና ያልመጠቀ ቁሜጭ ደረጃ ላይ መሆኑንም ጥሩ መረጃ መሆኑን ትገነዘባላችሁ።

እነዚህና የመሳሰሉ ብቻ ሳይሆኑ አማራ ተደራጅቶ እራሱን ከጥቃት እንዳይከላከል የሚጮኹ ጸረ አማራ ሆነው የምናያቸው ግለሰቦች ሌሎችም አንዲሁ "ግንቦት 7" ውስጥ የታቀፉ "የአማራ ተወላጅ ምሁራን" ነን የሚሉ "ማይሞችም" አሉ"። ለምሳሌ ተክሌ የተባለው ካናዳ የሚኖር ግለሰብ (አሁን ጠበቃ ነው አሉ!) "የአማራ ስም ያለው ፖለቲካ አመራር ውስጥ ወይንም መንግሥት ውስጥ በአመራር እንዳይፈቀድለት፤ ሓጎስ፤ ነገዎ፤ ወዘተ....የሚል ስም ያላቸውን መንግሥትነትን እና ፖለቲካውን በመሪነት መያዝ አለባቸው። ሰንደቃላማ ቢቃጠል So what!" የሚሉ ብዙ የወያኔ ሥራ እና መንገድ እንዲሁም ፖለቲካ እና ፖሊሲ ተግባራዊ የሚጥሩ አማራዎች ሆነው አማራን የሚጠሉ አሉ።

በግንቦት 7 አባልነት የተመዘገቡና ተምርን የሚሉ አማራ ነን የሚሉ እማ ደግሞ በታም እጅግ የከፉ ናቸው። በደረሰኝ መረጃ መሰረት በቅርቡ ከ....መጥተው ለስፖርት መዝናኛ በዓል መሪላንድ አማሪካ መጥተው እያሉ በኔ ላይ ጥላቻቸው በግልጽ በውይት መድረክ የገለጹ መሆናቸው እና፤ "ከትግሬት ይልቅ የአማራ ወኪል ሆኖ ነው የምናየው" ብለው ፤ እራሳቸው የከዱት የወላጆቻቸውን ስቃይ ስላጋለጥኩ ወላጆቻቸውን የሚሰድቡላቸውንና የሚዘልፉላቸውን የግንቦት 7 አመራሮች "ጀሌዎች" ሆነው በኔ ላይ ጥላቻቸው የሰነዘሩ ሰዎችም በስማቸው እና የት እንደሚኖሩ መረጃዎች ደርሰውኛል (እነኚህ ማራ ነን የሚሉ የተማሩ 'ማይሞች' ኢሳያስ ረድቶአቸው ወደ መንግስትነት ቢቀየሩ እኔን እንደ ወያኔ እና እንደ ደርግ ገርፈው ይሰቅሉኛል የሚል ግምት አለኝ)። እነዚህ ሁሉ አስመሳዮች፤ በወላጆቻቸው ስቃይ የሚያሾፉ፤ ደንታ የሌላቸው አሳዛኝ ፍጡራን ናቸው።

ለአማራው ስቃይ ተጠያቂው እና የወያኔ ጨዋታ እንዲቀጥል የሚያደርግ ተጫዋቹ 'የአማራ ምሁር ነው" ብዬ እንደምለው ሁሉ እንዳውም ትግሉን የገደሉት እነዚህ አማራዎች ናቸው የሚል ጓደኛዬም አለ። ለነዚህ ወላጆቻቸውን የከዱ አማራ ሆነው አማራን የከዱ በተቃወሚም ሆነ በወያኔ ስር ሚገኙ በትውልድ "አማራዎች" የሆኑ ዜጎች ለመግለጽ በትግርኛ አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ፡

እፈትወካ እየ እናበለ ዚጸልእ፤

እጸውም እንዳበለ ዚበልዕ፤

እህብ እየ እናበለ ዝኸልእ

እዝጊ ነዚኦም ይጸልእ።

ይላል። በግረድፍ ትርጉሙ

እወዳሃለሁ እያለ የሚጠላ፤

እጾማለሁ እያለ የሚበላ፤

እሰጣለሁ እያለ የሚነፍግ፤

እዝጊእነ/ፈጣሪ እነኚህን ይጠላል። ማለት ነው።

እነኚህ አማራውን ሳይወዱና በጥቃቱ ላይ ለመወያየት የማይፈቅዱ እና የሚሸሹ አማራዎች፤ "ፕሮፌሰር መስፍን አማራ የሚባል ነገድ የለም ስላሉ" ጸጉራቸው የሚያቆሙ 'አስመሳይ አማራዎችን' በግሌ በጣም ነው ጸጉሬን የሚያስቆሙት። እውነት እንነጋገር እና ፕሮፌሰር መስፍን "አማራው ሲበደል፤ ሲጠቃ፤ሲባረር፤ጭፍጨፋ ሲፈጸምበት" እየተከታተሉ ዘግበዋል፤ አጋልጠዋል፤ ታግለዋል። አሮምው ትግሬውም ሲጠቃ እንደዚሁ አድርገዋል። በትንተና ላይ ልዩነታችሁ ማስሰማት ተገቢ ቢሆንም፤ ለአማረው ሳይቆሙ ከርመው፤ አማራ የሚባል ነገድ የለም ብለው ፕሮፌሰሩ ተናገሩ፤ ተብሎ ሰማይን ለመምታት የሚቃጣችሁ "አስመሳዮች" መጀመሪያ እራሳችሁን መጠየቅ አለባችሁ።

አማራው የሚባል ነገድ "አለ" እያሉ አማራ "እንዳይኖር" የሚያጠቁ "የኦነግ፤ኦብነግ;ወያኔ እና ሻዕቢያ" ቡደድኖችን አማራውን ሲያጠቁ ወይንም ለወደፊቱ እንዳያጠቁት ምን እያደረጋችሁ ነው? አማራ ሆናችሁ፤ ወላጆቻችሁ ለምንድነው የተጸየፋችሗቸው? እኔ ኢትዮጵያዊ እንጂ አማራ አይደለሁም የሚባል ማምለጫ መስኮት ከየት ነው ያገኛችሁት?

አማራ የሚባል ነገድ የለም ካሉት ከፕሮፌሰሩ ታዲያ በምን ተለያችሁ? ያውም እሳቸው እማ አንዳንድ የማይጥመኝ ነገሮች ማድረጋቸውን "ሪዘርቨሽን" ቢኖረኝም፤ ለአማራው ቆመው ብዙ ነገር አድርገዋል። እናንተስ ምን አደረጋችሁ?

24 አመት አይተናችኋል። ለአማራው ምንም ስታደርጉ አልታያችሁም። አሁን ደርሳችሁ በፕሮፌሰሩ ላይ መጮሃችሁ ምን ለማለት ነው? አማራውን ከጥቃት ለመታደግ የቆሙት የሞረሽ ድርጅት መሪዎች እና አባሎች አንኳ ስም እየለጠፋችሁ ከወያኔ በባሰ መልኩ አማራው እንዳይደራጅ ለማፍረስ ስትሞክሩ አይተናችኋል፤ ታዝበናችኋል; ኢንተርኔት የዘገበው መረጃ አለ። "እወድሃለሁ እያለ አማራነቱን የሚጣላ አማራ" ጸጉሬን ከሚያቆሙት የመጀመሪያዎቹ እነኚህ ክፍሎች ናቸው። እውነት አውነት!!

ሌላ ቀርቶ በዘመነ ወያኔ ትግሬው ተጠቃሚ ነው ስል፤ እነሱ አጉል ለመወደድ ሲሉ አንዳርጋቸው የድምሕትን ድጋፍ ለማግኘት ሲል በአድርባይ ባሕሪው 'ትግሬው እንዳውም ከማንኛውም ዜጋ በኢኮኖሚ ያለበለጸገ ከደርግ ጊዜ በባሰ መልኩ የደኸየ ነው" ብሎ ከድምሕት/ ሻዕቢያ ቲቪ ያደረገውን ቃለ መጠይቁን እየደገሙ "ትግሬ አልተጠቀመም" ብለው በፀሓይ ቀርቶ በጭለማ መደበቅ የማይቻለውን ጠቀሜታ (ፕሪቪለጅ) ሃቁን እየሸሸጉ የሚዘላብዱ የተቃዋሚ መሪዎች እና ጋዜጠኞች በርካታዎቹ እነኚህ "አማራ የለም ስለተባሉ የሚጮኹ፤ ነገር ግን አማራ ሲጠቃ ዝም የሚሉ "ከሆዳም አማራዎች ጋር የሚደመሩ ሆዳም ያልሆኑ አመራዎች" በርካታ ናቸው።

ከወያኔ፤ከሻዕቢና ከኦነግ በባሰ መልኩ "ለአማራ ጥቃት ተባባሪ እና ተጨማሪ እንቅፋት የሆኑት ደግሞ አማራዎች እራሳቸው ናቸው።" በወያኔ ውስጥ የሚያገለግሉ እና በየፖለቲካ ድርጅቱ፤ በጋዜጠኛነት፤ በታቃወሚነት የተዳረጁ መሪዎች ተንታኞች፤ምሁራን እና አባሎች በብዛት ቢቆጠሩ "አማራዎች ናቸው"። እንዲህ ሆኖውም ታዲያ የአማራውን ጥቃት እና ስቆቃ፤ የወላጆቻቸው ስቃይ እየደበቁ "ስለ ጋዜጠኞች ስቃይ እና መታሰር" እስኪሰለቸን ድረስ ሲጮኹ፤ሲጽፉ፤ሲያስተጋቡ ይታያሉ። በጎን ግን አማራዎች ቤት ጅቦችና ተኩላዎች ገብተው ሽማግሌው፤ህጻናቱ እመጫቷ ከነደሟ እየተጎተተች የምትሞት፤መርዛማ መርፌ ተወግታ የምትሰቃይ መካን እና መድሃኒት ተከልክላ የታወረች እናትና አባት ሽማግሌ አማራውዎች በሚሊዮኖች ብርሃን ተጋርዶባቸው ፤ ከመኖር ወደ አለመኖር በሚሊዮን ሕዝብ ከምድረ ገጽ እንዲሰወር ሲደረግ፤ እየተለቀሰላቸው እና እየተዘገበላቸው ያለው ግን በብዛት ግለሰብ ጋዜጠኞ ች ብቻ ናቸው። ይህ ሁሉ አስመሳይ ጋዜጠኛ የሚናገረው አማርኛ ነው። አማራው ሲጠቃ ግን በሁለት ወር ወይንብ በስድስት ወር ለ10 ደቂቃ ዘግቦ፤ ወደ ጋዜጠኛ እና ወደ እስላም መሮዎች እስራት ነው የሚንደፋደፈውና የሚተነት ነው።

እነኚህ ቡድንተኛ ጋዜጠኞች (እኔ የፖለቲካ ማፊያ ጋዜጠኞች) ስለ አማራው ሳይሆን ስለ የሻዕቢያ አፈቀላጤ የነበረው አንዳርጋቸው ጽጌ ጉዳይ “ በሲኣይ ኤ ሰዎች እና በባንክ ባለጸጋዎች የተገነባውና የሚመራው አሻንጉሊቱ “የተባበሩት መንግስታት ድርጅት” ድረስ ተጻጽፈው ሞግተው እንዲሰማ ያደረጉለት ደግሞ አብዛኛዎቹ “አማራዎች” ናቸው (ግምባር ቀደም ጯኺዎችም አዳማቂዎችም፤ጀሌዎችም  አባዛኛዎቹ አማራዎች ናቸው)። ይታያችሁ!

አማራ የተባለ ማሕበረስብ ለ24 አመት ያለማቋረጥ ጥቃት ሲደርስበት ህፅናት በጅብ ሲበሉ፤ እመጫቶች ደማቸው ሳይደርቅ ከተኙበት መደብ እየተጎተቱ ሲጣሉ እና በሚባረሩበት “የዘር ጽዳት”  ግልጽ ወንጀል እየተደረገበት ባለው አገር፤ የሚነገረው ስለ አማራው ሰቆቃ ሳይሆን ‘ ስለ “የአማረውን ስነ ልቦና የሚነካ ፋሺስታዊ መጽሐፍ የጻፈ እና በመጻፉም “እኮራበታለሁ” ብሎ ለወዳጁ ለታማኝ በየነ በድፍረት ኢሳት ውስጥ ቃለ መጠይቅ አድርጎ፤ የተናገረውን አንዳርጋቸው ጽጌ የተባለ የኦሮሞ ተወላጅ በጥንት ወዳጆቹ በወያኔዎች ስለመታሰር እና ስለ ጦማሪዎች እና ጋዜጠኞች ሰቆቃ ነው የምናደምጠው!” ለምን? መልስ የሚፈልግ ጥያቄ ነው። ያውም አንድ ቀን ‘ፈጣሪ ጌታቸው ረዳን እርዳው ብሎታል መሰለኝ” ፤አማራው እንዲህ እየተገፋ “ሚዲያዎች ዝም ማለታቸው እጅግ አሳዝኖናል” ብሎ የተናገረውን አስታውሱ። እስከዚያው ድረስ ብቻየን ነበር እየጮህኩኝ አንደ አብድ ሲሰድቡኝ የነበሩ። ይህ ደግሞ ስለ አማራ ጠበቃ ማን አደረገው የሚሉኝ ነበሩ፤ አውድዮው አለኝ። ዜጋ መሆኔንም ዘንገተውታል። ስለ አማራ የመቆም መብቴም ኢትየጵያዊነቴን ያለ ፍረድ ቤት ችሎት ነጥቀውኛል።  እንደዚህ የሚሉኝ ደግሞ ኦነጎች ወይንም ወያኔዎች ብቻ ሳይሆኑ ‘እራሰቻው አማራ” ንን የሚሉትም ጭምር ናቸው። ለወላጆቻቸው ያልቆሙ ስለ እኔ በጎ ይናገራሉ የሚል ቅዠት የለኝም።

ይህ ስለ አማራው ግፍ ጎልቶ እንዳይወጣ እየተደበቀ ያለው “ኮንስፒራሲ/ተንኮል” ለአማራ ሕብረተሰበን የቆማችሁ አማራዎች እና ሌሎች ሰብአዊ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ኮንሰፒራሲው ሆን ተብሎ ወይስ ያለማወቅ የሚለውን መታገል እና መነጋገር አለባችሁ።

ጊዜ ከፈቀደ፤ በሚቀጥለው የሳምንት ጽሁፌ፤ ‘ሻዕቢያ ከወዳጁ ከወያኔ ጋር እንኳ በሰላም ለመኖር ያልፈለገ  የኢትዮጵያ ጠላት ‘ከግም ቡቴዎች’ ጋር ሰላም ይፈጥራል ብለው የሚያምኑ” “ከወያኔ ይልቅ ሻዕቢያ ኢትዮጵያዊ ነው” የሚሉን የ “ግም  ቡቴዎች” እምነት በጥልቀት እንመለከታለን። በኔ እምነት እነዚህ ያልበሰሉ ጅሎች “የኢቦላ ቫይረስ እና የኤድስ ቫይረስ፤ ሁሉም ካንዱ አንዱ የማይሻሉ ቫይረሶች መሆናቸውን ማየት ያቃታቸው ከቫይረስ ቫይረስ ሚያማርጡ” በሽተኞች በየፓልቶኩ ክርክሩን  እያራገቡት ነው።

እስከዛው ድረስ ብርሃኑ ነጋ ወደ አስመራ ማቅናቱ የሚመሰገን ሲሆን፤ የተስፋይ ገብረ አብ አዲስ መጽሀፍ ለማረም እና ሃሳብ ለመጨመር ምፅዋ ጉርጉሱም ሄዶ ሲዋኝ “በኢሳያስ ስር

ተደብቀው የወያኔ ድርብ ሰላዮች የሆኑ ሻዕቢያዎች ፎቶ አንስተው ዓይጋ ድረገጽ ላይ ተለጥፎ እንዳያሳዩን "የግም ቦቴ" ጀሌዎች ጸሎት ማድረግ አለባቸው። "አንገትህ ለይቶ የተቀረው አከላትህ ጤና ይስጥህ" ይላል መጥፎ ረጋሚ ይላሉ ትግሬዎች (ክሳድካ ከሊኡ ጥዕና ይሃብካ ይብል ከፉእ ረጋሚ)። ከዚህ ይሰውረን፤ አቦ! አሜን!

አመሰግናለሁ

ጌታቸው ረዳ